# የሲያትል ፓርኪንግ ተቆጣጣሪ ማነው፣ ለምን?

Seattle Department of Transportation (SDOT, የሲያትል የትራንስፖርት መምሪያ) የተሳሰሩ ሰዎች፣ ቦታዎችና ምርቶች ያሉባትን ብሩህ የሆነች ከተማ ለመደገፍ በማሰብ የመንገድ ላይ መኪና ማቆሚያን ያስተዳድራል፡፡

ለጎዳና ላይ መኪና መቆሚያ አገልግሎት (እንደዚሁም ለትራንዚት፣ ዕቃ ለማውረድና ለሌሎች በርካታ ነገሮች) የሚውል የመንገድ ዳር ቦታ በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈለግ ነገር ግን በአነስተኛ መጠን የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህ የሰዎችና የዕቃዎች እንቅስቃሴ የተስተካከለ እንዲሆን ለማድረግ፣ የቢዝነስ አካባቢዎችን ጠቀሜታ ለመደገፍና ለኑሮ ምቹ የሆኑ አካባቢዎችን ለመፍጠር በማሰብ ተፎካካሪ ፍላጎቶችን በጥንቃቄ እናመጣጥናለን፡፡

ስለዚህም የመንገድ ዳር መኪና መቆሚያዎችን የምንቆጣጠረው፣ ክፍያ የሚጠየቅባቸው የመኪና ማቆሚያ፣ መጫኛና በቢዝነስ አካባቢዎች ለአጭር ጊዜ የመኪና ማቆሚያ እንደዚሁም በመኖሪያ አካባቢዎች የተገደቡ የመኪና ማቆሚያ ቀጠናዎችን እናመቻቻለን፡፡ ከሲያትል ፖሊስ መምሪያ የፓርኪንግ ሕግ ማስከበር ጽ/ቤት፣ ከፕላኒንግና ዴቨሎፕመንት (ከመንገድ ውጭ ላለ ፓርኪንግ)፣ ከሲያትል አውራጃ ፍ/ቤትና ከፋይናንስና አስተዳደራዊ አገልግሎት መምሪያ ጋር አብረን እንሰራለን፡፡

## የፓርኪንግ ቲኬቶች

የፓርኪንግ ቲኬት እንዲሰጥዎ ከሚያደርግ ሁኔታ እንደሚርቁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቲኬት ከተሰጠዎ፣ በ15 ቀናት ውስጥ ቅጣትዎን መክፈል ይችላሉ፡፡ የቅጣት ክፍያውን ለመክፈል አራት አማራጮች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ አማራጮችም ከቲኬቱ በስተጀርባ ላይ ተጽፈዋል፡፡

**አብሮ በተሰጠዎ ኤንቨሎፕ አድርገው በፖስታ ለመላክ፡**
Municipal Court of Seattle, PO Box 34987,
Seattle, WA 98124-4987

**በስልክ፡** (206) 233-7000

**ኦንላይን፡** www.seattle.gov/courts

**በአካል፡** Municipal Court of Seattle,
600 5th Avenue, ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8 AM–5 PM

## የፍ/ቤት ቀጠሮዎች

ቲኬቱ የተሰጠኝ በስህተት ነው ብለው ካመኑና ቲኬት መሰጠቱን በመቃወም ዳኛ ፊት ለመቅረብ ከፈለጉ፣ የመቃወሚያ ችሎት እንዲዘጋጅልዎ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

የደንብ ጥሰት መፈጸምዎን አምነው ነገር ግን የገንዘብ ቅጣት መጠን እንዲቀንስልዎ ዳኛውን ለመጠየቅ ከፈለጉ፣ የቅጣት ማቅለያ ችሎት እንዲዘጋጅልዎ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡** (206) 684-5600 ወይም
www.seattle.gov/courts/hearings/hearinginformation.htm

## ያልተከፈሉ ቲኬቶች

አራት ወይም ከዚያ በላይ ያልተከፈሉ የፓርኪንግ ቲኬቶች ያሉባቸው ተሽከርካሪዎች እንዳይንቀሳቀሱ የሚያደርግ መሳሪያ ይገጠምባቸዋል፡፡ አንዴ ይህ መሳሪያ ከተገጠመ፣ በ48 ሰዓት ውስጥ ቲኬቶቹና ሌሎች ክፍያዎች ካልተከፈሉ ተሽከርካሪው እየተጎተተ ይወሰዳል፡፡ ተጨማሪ መረጃ፡ www.seattle.gov/scofflaw




## የመንገድ ዳር የክፍያ መኪና ማቆሚያ

በክፍያ የመኪና ማቆሚያ አገልግሎት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከ 8 AM እስከ 6 PM ወይም 8 PM ድረስ ነው፡፡ የክፍያ መጠንና ሰዓት በየዓመቱ የሚወሰን ሲሆን እንደየአካባቢው ሁኔታ የሚለዋወጥ ይሆናል፡፡ አረንጓዴ ቀለም ያለው የክፍያ ፓርኪንግ ምልክት የተሻለ ዋጋን ያመለክታል፡፡ ሰማያዊ ቀለም ያለው ምልክት After 5 ከሚል ምልክት በኋላ ካዩ የምሽት ክፍያ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ትራፊክ የሚበዛባቸው በርካታ መንገዶች ጠዋትና ማታ ላይ በመንገድ ዳር መኪና ማቆምን ይገድባሉ፡፡

ሁሉም ባለክፍያ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ሞባይል ክፍያ አላቸው፡፡ ከ app store ላይ የ PayByPhone መተግበሪያን አውርደው ፈጣንና ምቹ የፓርኪንግ ክፍያ ለመክፈል የሚያስችልዎ አካውንት ይፍጠሩ፡፡

## የግንኙነት መንገዶችና ዲጂታል መሳሪያዎች

ለተጨማሪ መረጃ፡
(206) 684-ROAD (7623)

አጣዳፊ ላልሆኑ ጉዳዮች የፓርኪንግ ሕግ አስከባሪ ኦፊሰር ለማነጋገር ከፈለጉ፡
(206) 625-5011

ባለቤት አልባ ተሽከርካሪዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡
(206) 684-8763

መኪናዎ ከሕዝባዊ መንገድ ላይ ተጎትቶ ከተወሰደ፡
(206) 364-2000 ወይም ይህን ይጎብኙ
www.seattleimpound.com

የ SDOT የፓርኪንግ መረጃ ለማግኘት፡
www.seattle.gov/parking

በስማርት ስልክ ለተባ የዳውንታውን ፓርኪንግ ካርታ፡
www.DowntownSeattleParking.com

ለSDOT የአሁን ጊዜ የጋራጅ ቦታ መረጃ ለማግኘት፡
www.seattle.gov/transportation/epark/mobile

# መኪና እዚህ ማቆም እችላለሁ?

ምልክቶቹን ይወቁ፣ ቲኬት እንዳይሰጥዎ ይጠንቀቁ፣ ሕጉን አክብረው መኪና ያቁሙ፡፡
**ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ እናሳይዎታለን፡፡**

Seattle Department of Transportation

11.2016

# መኪና ማቆም ክልክል ነው

## ጠባብ መተላለፊያ መንገዶች

በጠባብ መተላለፊያ መንገዶች ላይ ለረዥም ጊዜም ሆነ ለአጭር ጊዜ መኪና አያቁሙ:: የንግድ ተሽከርካሪዎች እስከ 30 ደቂቃ ለሚሆን ጊዜ ቆመው መጫን/ማውረድ ይችላሉ::

## ቁምና ቅድሚያ ስጥ

ቁምና ቅድሚያ ስጥ የሚል ምልክት ባለበት ቦታ በ30 ጫማ ርቀት ውስጥ ወይም በእግረኛ ማቋረጫ 20 ጫማ ርቀት ውስጥ መኪና አያቁሙ::

## የውስጥ ለውስጥ መንገዶች

የውስጥ ለውስጥ መንገዶች 5 ጫማ ርቀት ውስጥ መኪና አያቁሙ:: ነዋሪዎች/የቤት ባለቤቶች በውስጥ ለውስጥ መንገድ እያንዳንዱ ጎን በኩል እስከ 5 ጫማ ቢጫ ቀለም መቀባት ይችላሉ::

## የእሳት ማጥፊያ ፈሳሽ ምንጭ

የእሳት ማጥፊያ ፈሳሽ ምንጭ ካለበት ቦታ በ15 ጫማ ርቀት መኪና አያቁሙ::

## የእግረኛ መንገዶች እና የአትክልት መትከያ ቦታዎች

በእግረኛ መንገዶች ላይ እንደዚሁም በእግረኛ መንገድና በመኪና መንገድ መካከል ባሉ አካፋይ ቦታዎች ወይም አትክልት መትከያ ቦታዎች ላይ መኪና አያቁሙ::

## መስቀለኛ መንገዶች እና የእግረኛ ማቋረጫዎች

በመስቀለኛ መንገድ፣ በእግረኛ ማቋረጫ ወይም የእግረኛ ማቋረጫ አካባቢ በ20 ጫማ ርቀት ላይ መኪና አያቁሙ፤ የ"T" መስቀለኛ መንገዶችን ይጨምራል:: የፓርኪንግ ምልክት አለመኖሩን ያረጋግጡ:: የእግረኛ ማቋረጫዎች ምልክት ያላቸው (ቀለም የተቀቡ) ወይም ምልክት የሌላቸው (ቀለም ያልተቀቡ) ሊሆኑ ይችላሉ::




## መኪና ከቆመ ተጎትቶ የሚወሰድባቸው ቦታዎች

በእነዚህ ቦታዎች ወይም ቀይ ቀለም በተቀቡ ማናቸውም ቦታዎች መኪና አያቁሙ::



## ማቆም የማይቻልባቸው ቦታዎች

በእነዚህ ቦታዎች መኪና አያቁሙ::




## በጊዜያዊነት ማቆም የማይቻልባቸው ቦታዎች

ምልክቱ ላይ በተለጠፉ ቀናትና ሰዓታት መኪና አያቁሙ:: ጥያቄዎች ሲኖርዎት ለደንበኛ አገልግሎት ቢሮ በስልክ ቁጥር (206) 684-ከተማ ይደውሉ::

## ሌሎች የተለዩ ቦታዎች

በአውቶቡስ ማቆሚያ፣ በታክሲ ማቆሚያ፣ በቻርተር አውቶቡስ ማቆሚያ ወይም በመኪና ማጋሪያ ቦታዎች ላይ መኪና አያቁሙ::

## የንግድ እና ትላልቅ ተሽከርካሪዎች

በኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ውስጥ ከእኩለ ሌሊት እስከ 6 AM ባለው ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ከ80 ኢንች በላይ ስፋት ያለውን የጭነት መኪና/ባለ ተሳቢ በማንኛውም መንገድ ወይም ጠባብ ጎዳና ላይ አያቁሙ::

5 ጫማ — የውስጥ ለውስጥ መንገድ

15 ጫማ — የእሳት ማጥፊያ ፈሳሽ ምንጭ

20 ጫማ — የእግረኛ ማቋረጫ

30 ጫማ — የቁም/ቅድሚያ ስጥ ምልክት

## በምን ያህል ቅርበት ማቆም እችላለሁ?

# መኪና ማቆም አንዳንድ ጊዜ ይፈቀዳል




## የአካል ጉዳተኞች መኪና ማቆሚያ

ለአካል ጉዳተኞች በተለዩ መኪና ማቆሚያዎች አያቁሙ ወይም ፈቃድ ይጠቀሙ:: 1) እርስዎ ወይም ተሳፋሪዎ አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ በስተቀር፣ እና 2) ተሽከርካሪዎ የፀና የአካል ጉዳተኝነት ምልክት፣ ሰሌዳ ቁጥር ወይም መለያ ቁጥር ካልተለጠፈበት በስተቀር:: ይህን ቦታ ያለአግባብ መጠቀም እስከ $450 ድረስ ያስቀጣል::




## የክፍያ መኪና ማቆሚያ

በክፍያ ጣቢያ ወይም በስልክ ክፍያ መክፈል ያስፈልጋል:: 'After 5' ከሚል ምልክት ቀጥሎ የሚኖር ሰማያዊ ምልክት ከ5 PM በኋላ የ3 ደቂቃ ጊዜ ገደብ መኖሩን የሚጠቁም ነው:: አረንጓዴ ምልክት የሚጠቁመው ደግሞ በአነስተኛ ክፍያ ወይም ለረዥም ጊዜ ማቆም የተፈቀደ መሆኑን ነው::




## የተገደበ የመኪና ማቆሚያ ክልል (RPZ)

ተሽከርካሪዎ የ RPZ ፈቃድ ካለው፣ እስከ 72 ሰዓታት ለሚቆይ ጊዜ በተፈረሙ የ RPZ መንገዶች ላይ መኪና ማቆም ይችላሉ:: ፈቃዱ ከሌለዎ፣ በተለጠፈው የሰዓት ገደብ ይወሰናሉ:: ይደውሉ፡ (206) 684-5086.




## ትራፊክ የሚበዛባቸው ሰዓታት

ምልክቱ ላይ በተለጠፉት ሰዓታት መኪና ካቆሙ መኪናዎ በክሬን ተጎትቶ ይወሰዳል:: የተገደቡ ሰዓታት የሚቀያየሩ በመሆኑ ምልክቶቹን በጥንቃቄ ይመልከቱ::




## በጊዜ የተገደቡ ቦታዎች

የተለጠፈውን የሰዓት ገደብ አክብረው መኪና ያቁሙ:: መኪናዎን ከብሎኩ ውጭ ባለ ቦታ ማቆም አለብዎ (በመንገዱ ሁለቱም አቅጣጫዎች)፡ ለምሳሌ፣ ቀጥሎ ወዳለው ብሎክ ወይም በማዕዘኑ አካባቢ::




## መጫንና ማውረድ

ሁሉም ተሽከርካሪዎች ምልክቱ ላይ በተለጠፈው ሰዓት መጫን/ማውረድ አለባቸው::
(የመንገድ ጠርዝ ቀለም፡ ቢጫ::)




## ተሳፋሪ መጫን

ሁሉም ተሽከርካሪዎች ምልክቱ ላይ በተለጠፉት ሰዓታት ለ3 ደቂቃ ያህል ቆመው ተሳፋሪ መጫንና ማውረድ ይችላሉ::
(የመንገድ ጠርዝ ቀለም፡ ነጭ::)




## የጭነት መኪና መጫኛና ማውረጃ

የጭነት መኪና ሰሌዳ ቁጥር ያላቸው ተሽከርካሪዎች ብቻ ምልክቱ ላይ በተለጠፉት ሰዓታት ውስጥ መጫን/ማውረድ ይችላሉ::
(የመንገድ ጠርዝ ቀለም፡ ቢጫ::)




## የንግድ ተሽከርካሪ መጫኛ ክልል (CVLZ)

የንግድ ተሽከርካሪዎች ብቻ እስከ 30 ደቂቃ ለሚሆን ጊዜ መጫን/ማውረድ ይችላሉ:: ክፍያ መክፈል ወይም የፀና CVLZ መያዝ አለብዎ:: ይደውሉ፡ (206) 684-5103.
(የመንገድ ጠርዝ ቀለም፡ ቢጫ::)

## ሌሎች ሁኔታዎች

**የሰሌዳ ቁጥርና መለያ ቁጥሮች**

የመኪናዎ የፊት ወይም የኋላ ሰሌዳ ሳይኖር ወይም የአገልግሎት ዘመኑ ያለቀ መለያ ቁጥር ይዘው መንገድ ዳር አያቁሙ::

**የ72 ሰዓት ደንብ**

ተሽከርካሪዎን በአንድ ብሎክ ስር ከ72 ሰዓት በላይ አያቁሙ፣ ካለበለዚያ መኪናው ባለቤት አልባ ተደርጎ ስለሚቆጠር ቲኬት ይጻፍበታል ወይም በክሬን ተጎትቶ ይወሰዳል::